የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ግንቦት 15 ቀን 2000 ዓም

## ለወያኔ ቡድን የማደናገር ዘመቻ ሰለባ አንሁን

የሀገርን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሰጥቶ ካበቃ በኋላ ክህደቱ ሲጋለጥ በመጀመሪያ ዜናው ሀሰት ነው ብሎ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ በኩል ሲክድ፣ ቀጥሎ ደግሞ በጭፍሮቹ አማካይነት መረጃ ይቅረብ ብሎ ሲያታክት፣ ከዚያም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የተፈረመ ሰነድን በስራ ለማዋል ጣርን ወዘተ ወዘተ ብሎ ሲያደናግር ከቆየ በኋላ አሁን ደግሞ በዋሾው ቁንጮው አማካይነት ያስተላለፈው መልዕክት ማንም ኢትዮጵያዊ ከመሬቱ የማይፈናቀልበት ስምምነት አደረግን የሚል ነው:: ከሀገራቸው መሬትና እርሻ በሱዳን ወታደር ተፈናቅለውና ተጠልፈው ለሱዳን እስር የተዳረጉት ዜጎች ለዚህ ቀጣፊ የወያኔ መሪ ወይ ኢትዮጵያዊ አይደሉም ወይም ምትሀት ናቸው ማለት ነው::

ሁሉም ዜጋ ሊያውቅ የሚገባው አንድ መሰረታዊ ሀቅ ሱዳንና ወያኔ ተደራድረው ሱዳን ለኢትዮጵያ የሚለቀው መሬት ካለመኖሩ ሌላ የወያኔ አገዛዝ ዋና ዓላማ ሱዳን ለዘመናት ሲመኝ ግን ሊያገኝ ያቃተውን የሀገር መሬት ለሱዳን ማስረከብ መሆኑን ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የወያኔው የክህደት ቁንጮ ለሱዳን መሬት ብንሰጥም የሚፈናቀል አይኖርም ማለቱ፣ አንድም ዓይን አውጣ ውሸት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ የተወሰነ ቆላ መሬት በወባ በሽታ የተነሳ የሰፈረ ገበሬ ባይኖርም እንኳን፥ የሀገር መሬት የሀገር መሬት ነውና ሰፋሪ የለበትም በሚል ለማንም ባዕድ የሚቸር አለመሆኑን የወያኔ ቡድን መካዱን ወይም አውቆ መርሳቱን የሚያመለክት ነው:: ሀገር ወዳዶች በሀገር መሬት የለም ዋዛ ብለው መነሳሳት በመጀመራቸው የተደናገጠው የወያኔ ቡድን የማደናገር ዘመቻውን ከማጧጧፉ ባሻገር የተቃውሞውን እንቅስቃሴ ከውስጥ ሆኖ ለማኮላሸትና ለመከፋፈል በተፋጠነ መልክ እየተሯሯጠ ነው:: በዚህም መልክ ለሀገር የተቆረቆሩ መስለው ግን መሰረተ ቢስ "መረጃ"ን እያወጡ የተቃውሞውን ጥረት ከንቱና ዋሾ ለማስመሰል የሚቅበዘበዙ ሰርጎ ገቦችን አሰማርቷል:: የወያኔ አገዛዝ የክህደት ድርጊትንና የሱዳንንም ህገወጥ እርምጃ በመቃወም ዓለም አቀፍ ሰልፎችንም ለማስቆም ወይም ለማደናቀፍ እንዲሁ ኮሚቴዎችን ሰርገው ገብተው የሚያተራምሱ ቡደኖችንና ግለሰቦችን በማሰማራት ላይ ነው:: ይህን ሁሉ ጠንቅቆ በመረዳት የወያኔን አገዛዝ መሰሪ የማደናገርና የመከፋፈል ዘመቻ በጋራ ለማሸነፍ ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ መነሳት፣ መታገል አለበት:: ኢሕአፓ በዚህ ረገድ ያልተቋረጠ ፀረ ወያኔ ትግሉን ያካሂዳል::

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France